January 26, 2012

በኣላህ ስም እጅግ በጣም ሩሕሩሕ በጣም ኣዛኝ በሆነው።

የዐወሊያ ተማሪወችን እንቅስቃሴና በቅርቡ ሕገወጡን መጅሊስ በሕጋዊ መንገድ ለማስውገድ እንዲያስትባብር የተመረጠዉን ኮሚቴና ለማድርግ የወሰነውን ሕጋዊ እንቅስቃሴ በመደገፍ የቶሮንቶና ኣካባቢውን ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ለማስትባበር በኦክቶበር 30፣ 2010 ከትመረጠው ጊዜኣዊ ኣስትባባሪ ኮሚቴ የተሰጠ የድጋፍ መግልጫ።

የኣወሊያ ተማሪውች ያሳዩት የትገል ስልትና የኣመራር ብስለት የኣወሊያን የትምሕርት ተቃም መጅሊስ ሊርጭበት ከፈለገው መርዝ ያስቀመ ትግል ብቻ ሳይሆን፤ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ለሕገመንግስታዊ መብታችው፤ ለሚያደርጉት ትግል ታላቅ ምሳሌ የሆነና ሙስሊሙ ከነበረበት እንቅልፍ ያነቃ፤ በሕግዊ መንገድ ኣንድና ብቸኛ ድርጅቱን (መጅሊሱን) እስላማዊ እውቀትና ኣደብ ባላቸው መሪወችና በሕዝብ በተመረጡ መሪወች እንዲተካ ለሚደረገው ጥረት በር የከፈተ ታላቅ እንቅስቃሴ ነው። ስለሆነም፤ በቶሮንቶና ኣካባቢዋ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ኣስተባባሪ ኮሚቴ ያኣወሊያ ተማሪዎችን ላደረጋችሁት ጥረት ኣላህ (ሱወ) ምንዳችሁን እንዲከፍላችሁ ዱአ እያደረገን የትግላችሁ ኣጋርና ደጋፊ መሆናችንን እንገልጻለን።

በመቀጠልም የኣወሊያን ተማሪወች በመደገፍ በኣወሊያ ምስጊድ በጁማ ቀን ሙስሊሙ በመሰባስብ መጅሊስ ሙስሊሙ በመረጣቸው ሙስሊም ምሁራን እንዲመራን ከኣህባሽ የበከለ ረእዮት ጠርቶ የሙስሊሙ መከታና ዬእስልምና ጠበቃ እንዲሆን፤ መንግስት በሃይማኖታችን ጣልቃ መግባቱን እንዲያቆም፤ ሙስሊሙም በኣገሩ ዬእድገትና ብልጽግና እቅድ ተሳትፎውን እንዲያበረታታ የተደረገዉን ውይይትና ለማስትባበር የተመረጠውን ጊዚያዊ ኣስተባባሪ ኮሚቴ ደጋፊ መሆናችንን ለማስገንዘብ እንፈልጋለን።

በዚህ ኣጋጣሚም የኢትዮጵያ መንግስት ይሙስሊሙን ብሶት በኣንክሮ በማዳመጥ ኣንድና ብቸኛ ድርጅቱን ሙስሊሙ በመረጣቸው መሪዎቹ እንዲተካ መንገዱን ያስተካል ዘንድ እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ መንግስት ኣጽንኦት ሰጥቶ እንዲያየው የምናሳስበው ዋና ጉዳይ፤ ዛሬ መጅሊሱን እየመሩ ያሉ ግለሰቦች ሕዘብ ያልመረጣቸው፤ በሕዝብ ያልተውከሉ፤ የሙስሊም ኣደብና እስላማዊ እውቀት የሌላቸውና የሕዝቡን የልብ ትርታ የማያዳምጡ፤ የፖሊቲካ ካድሬዎች በመሆናቸው፤ የሙስሊሙ ድጋፍ የሌላቸው እንዲሁም መንግስትና የሙስሊሙን ሕብረተሰብ የሚያጋጭ እንቅስቃሴ በማደረግ ላይ ያሉ በመሆኑ፤ ከነዚህ ጥቂት ግለሰቦች ጋር ኣጋር ሆኖ መስራት ለኣገር ልማትና እድገት እንዲሁም ለሰላምና መረጋጋት የሚብጅ እንደማይሆን ተረድቶ ከብዙሃኑ ሙስሊም ጋር እንዲሰለፍ ኣጥብቀን ለማስገንዘብ እንፈልጋለን።

የኣወሊያ ተቃም ተማሪዎችና የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕዝብ የኣገራችን ሕግመንግስት ለሕዝቦቻ ያጎናጸፈውን ዬምነትና ነጻነትና የዜግነት የመደራጀት መብት ለማስከበር በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ለምታደርጉት ትግል ከጎናችሁ መሆናችንን እንገልጻለን።

ኣላህ (ሱወ) ከናንተ ጋር ይሁን!!!

**የቶሮንቶና ኣካባቢውን ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን**

**ሙስሊሞች ጊዜኣዊ ኣስትባባሪ ኮሚቴ**